- Camp Coordination and Camp Management
- Child Protection
- Food Security and Agriculture
- Housing, Land and Property
- Education
- Health
- Humanitarian Mine Action
- Nutrition
- Livelihoods
- Protection
- Shelter, Settlement and Recovery
- Water, Sanitation and Hygiene
- Humanitarian Operati[…] Support Sectors

ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች ድጋፍ ለማድረግ የሚረዳ መመሪያ

በአካባቢዎ የጾታ ተኮር ጥቃት (GBV) ተዋናይ በማይገኝበት ጊዜ

ሰብአዊ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች የሚሆን ዝርዝር በኪስ የሚያዝ መመርያ

Ministry of Women Children and Youth
UN WOMEN
unicef
UNFPA

ይህ የጾታ ተኮር ጥቃት (GBV) የኪስ መመሪያ እና ተጓዳኝ የሞባይል መተግበሪያ ስሪት እ.ኤ.አ. በ 2020 ከ UNICEF እና UN Women በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የተሰራ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ በጸደቀው በኤጀንሲዎች መካከል ባለ የመርጃዎች ስብስብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለኢትዮጵያ አውድ እንዲመች ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡ የኪስ መመሪያውን አውድ የማሻሻል እና የመተርጎም ሥራ የተመራው በ UNICEF ፣ UNFPA ፣ UN Women እና በሴቶች ፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚንስቴር እንዲሁም ከ International Rescue Committee, the Child Protection and Gender Based Violence Area of Responsibility, and the PSEA Network በኢትዮጵያ በተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ ነው፡፡ የቅብብል መርጃዎችን ፣ አካባቢያዊ ቃላቶችን እና ከኢትዮጵያ አውድ አንጻር ተጨማሪ መረጃዎችን ማካተት ቁልፍ ማሻሻያዎች ነበሩ፡፡

ይህ የጾታ ተኮር ጥቃት የኪስ መመሪያ ስሪት በድንበር የለሽ ተርጓሚዎች (Translators Without Borders) ወደ አማርኛ ፣ ኦሮሚኛ ፣ ትግርኛ እና ሶማሊኛ ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን በሴቶች ፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ፈቃድ አግኝቷል፡፡

Camp Coordination and Camp Management

Child Protection

Food Security and Agriculture

Housing, Land and Property

Education

Health

Humanitarian Mine Action

Nutrition

Livelihoods

Protection

Shelter, Settlement and Recovery

Water, Sanitation and Hygiene

Humanitarian Operations Support Sectors

የኪስ መመሪያው ምንድነው?

የኪስ መመሪያው እና ደጋፊ ቁሳቁሶቹ [1] የሚሰጠው **መረጃ ለሁሉም ሰብአዊ ስራ ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ሲሆን** የሚከተሉት ላይ ያተኩራል:

- ጾታ ተኮር ጥቃት (GBV) የደረሰበትን/የደረሰባትን ግለሰብ እንዴት መደገፍ ይቻላል?
- የጾታ ተኮር ጥቃት (GBV) ልምዳቸውን ለእርስዎ የሚገልጹ
- የጾታ ተኮር ጥቃት ተዋናይ (የጾታ ተኮር ጥቃት ቅብብሎሽ ወይም የጾታ ተኮር ጥቃት የትኩረት ነጥብን ጨምሮ) በሌለበት አውድ ውስጥ።

የኪስ መመሪያው ተጨማሪ ጉዳት ሳይደርስ የጾታ ተኮር ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች መሰረታዊ ድጋፍ እና መረጃን ለመስጠት ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ይጠቀማል። በጾታ ተኮር ጥቃት ባለሙያ ድጋፍ እና ጥቃት የደረሰባቸውን ግለሰቦችን ባማከለ ሁኔታ ይህንን መርጃ ከአከባቢዎ ሁኔታ ጋር እንዲመች አርገው እንዲያሻሽሉት እናበረታታለን።

ምንም እንኳን የኪስ መመሪያው የሥነ-ልቦና የመጀመሪያ እርዳታ ማዕቀፍን (መዘጋጀት ፣ መመልከት ፣ ማዳመጥ እና መገናኘት) ቢጠቀምም የሥነ-ልቦና የመጀመሪያ እርዳታ ላይ ቀደም ብሎ እውቀት መያዝን ወይም ስልጠና መውሰድን አይጠይቅም። የተቀናጀ የሥነ-ልቦና የመጀመሪያ እርዳታ (PFA) ስልጠና ይበረታታል።

[1] ከኪስ መመሪያው ጋር አብሮ የጀርባ ማስታወሻ እና ጠቃሚ ምክሮች የተካተቱበት / እንዴት ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ መመርያ አብረው ይገኛሉ።

ይዘት

ክፍል	ገጽ	ጿቂቃዎች
ቁልፍ መልዕክቶች	2 & 3	አፋጣኝ መመሪያ
የውሳኔ ዛፍ	4	
የመረጃ ሰነድ በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ የተዘጋጀ	6	
መደረግ የሚገባቸው ፣ መደረግ የማይገባቸው እና ምን መናገር እደሚገባ		
መመልከት	8	
ማዳመጥ	9	
መገናኘት	10 እና 11	
ዝርዝር መመርያ		ዝግጅት እና እውቀት እና ክህሎቶችን ምላሽ ለመስጠት መገንባት
ድጋፍ መሻት እና PSEA	12	
መዘጋጀት፣ መመልከት፣ማዳመጥ እና መገናኘት	13 - 16	
ህጻናት እና በጉርምስና እድሜ የሚገኙ ታዳጊዎች	17 - 20	ከ 18 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት እና በጉርምስና እድሜ ለሚገኙ ታዳጊዎች ፈጣን መመሪያ

ቁልፍ መልዕክቶች

ሁሌም በመጀመርያ የGBV ባለሙያን ያነጋግሩ፤ በአካባቢዎ የGBV አገልግሎቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመረዳት አንዳንድ አገልግሎቶች የስልክ መስመሮችን ፣ የሞባይል መተግበሪያን ወይም ሌላ የርቀት ድጋፍን ሊወስዱ ይችላሉ።

ስለ ሌሎች አገልግሎቶች ግንዛቤ ይኑሮት፤ በተለይም በአካባቢዎ ስለሚገኙ በሰብአዊ አጋሮች እና በመንግስት የሚሰጡ እንደ ጤና ፣ የሥነ-ልቦና እና ማኅበራዊ ድጋፍ ፣ መጠለያ ፣ የህግ ድጋፍ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ አቅርቦቶችን ይለዩ፡ ፡ እንደ በመሰረታዊ ደረጃ በሚሰጡ፣ በእምነት ላይ በተመሰረቱ፣ በሴቶች በሚመሩ ድርጅቶች እና ቡድኖች እና በአካል ጉዳተኞች አገልግሎት ድርጅቶች ባሉ በማኅበረሰቦች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ከግምት ያስገቡ።

ኃላፊነቶን ያስታውሱ:: ከፍርድ ነፃ የሆነ የሚያዳምጥ ጆሮ ያቅርቡ። በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃን ያቅርቡ:: ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ የራሱን / ሷን ምርጫ ይወስን / ትወስን። ማስተዳደር / መስራት የሚቻሉትን ይወቁ::በአካባቢዎ የ GBV ተዋናይ ባይኖርም ተጨማሪ ትኩረት እና ድጋፍ የሚሹ ጥቃት የደረሰባቸው ግለሰቦችን መርዳት የሚችሉ እንደ ህጻናት ጥበቃ ወይም የአእምሮ ጤና ባለሙያ አይነት ያሉ ሌሎች አጋሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ከማንኛውም ሰው ጋር ከማገናኘትዎ በፊት ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ ፈቃድ ይጠይቁ። ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ አይሆንም ካለ / ች አያስገድዱ።

GBV ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎችን በንቃት አይለዩ ወይም አይፈልጉ። አንድ ግለሰብ እርዳታን ከጠየቀ/ች ራስዎን ዝግጁ ያድርጉ።

ተልእኮዎን ያስታውሱ:: ሁሉም ሰብአዊ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች በጾታ፣ በወሲባዊ ዝንባሌ፣ በጾታ ማንነትን ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካል ጉዳት ሁኔታ፣ በዕድሜ ፣ በብሔር/ጎሳ/የዘር/ እምነት፣ ወንጀሉን በፈጸመው ሰው ማንነት እና ወንጀሉ በተፈጸመበት ሁኔታ ላይ ሳይመሰረቱ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ፣ አድልኦ የሌለበት እና አግላይ ያልሆነ እርዳታ ድጋፍ ለሚሹ ሰዎች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

የሚጠቀሙት **ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ ያማከለ አካሄድ ይሁን፤** ለዚህም የሚከተሉትን ያድርጉ፡

- **አክብሮት**:የሚወስዷቸው ሁሉም ድርጊቶች ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ ምርጫዎች፣ ምኞቶች መብቶች እና ክብር በማስጠበቅ መመራት አለባቸው።
- **ደህንነት**:ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ደህንነት ቁጥር አንድ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።
- **ምስጥራዊነት**:ሰዎች ታሪካቸውን ለማን እንደሚናገሩ ወይም መናገር እንደሌለባቸው የመምረጥ መብት አላቸው። ምስጥራዊነትን መጠበቅ ማለት ማንኛውንም መረጃ ለማንም አለማጋራት ማለት ነው።
- **አድልዎ አለማድረግ**: ድጋፍ ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው እኩል እና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት።

የጤና አገልግሎቶች ካሉ ሁልጊዜ ባሉ አገልግሎቶች ላይ መረጃ ይስጡ። የሚያውቁትን ያጋሩ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ የማያውቁትን ያብራሩ። ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ እነሱን ማግኘት እንደሚፈልግ ራሱ/ሷ ይወስን/ትወስን፡ ፡ በ 72 ሰዓታት ውስጥ ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት ማግኘት በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖችን (STIs) እንዳይተላለፉ እንዲሁም በ120 ሰዓታት ውስጥ ደግሞ ከተደረገ ደሞ አላስፈላጊ እርግዝናን ይከላከላል።

ፈቃደኛነቱ ካለ እና ከተንከባካቢዎቻቸው ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ አደጋን ወይም ውጥረትን የማይፈጥር ከሆነ ሕጻናት እና የአካል ጉዳተኞች ተንከባካቢዎቻቸው ሳይኖሩ ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት እንዲችሉ እድሉን ያቅርቡ::

ለ
ህጻናት እና
በጉርምስና እድሜ
ለሚገኙ ታዳጊዎች
ወደ ገጽ
17 ይሂዱ።

አንድ አዋቂ ወንድ ወይም ህጻን ወንድ ልጅ ከተደፈረ ተመሳሳይ ጾታ/ ወንድ አፍቃሪ ነው ማለት አይደለም። በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት በኃይል ላይ እንጂ በአንድ ሰው የወሲብ ዝንባሌ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ሆኖም ጥቃት በአንድ ሰው እውነተኛ ወይም በሰዎች ዘንድ እውነተኛ ነው ተብሎ በሚታሰበው ወሲባዊ ዝንባሌ ምክንያት ሊፈጸም ይችላል።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በወሲባዊ ዝንባሌያቸው እና/ወይም በጾታ ማንነታቸው ምክንያት ለጉዳት እና ጥቃት ተጋላጭነታቸው ከፍ ያለ ነው። ንቁ ሆነው ያዳምጡ እንዲሁም ጥቃት ለደረሰባቸው ግለሰቦች ድጋፍን ይፈልጉ።

ማንኛውም ሰው ማለትም የትዳር አጋርን፣ የቅርብ ጓደኛን፣ የቤተሰብ አባልን፣ ተንከባካቢን፣ አማትን፣ እንግዳ ሰውን፣ ወላጅን፣ አገልግሎት ሰጪን ወይም ገንዘብን ወይም እቃዎችን ለወሲባዊ ድርጊት የሚቀይር ሰውን ጨምሮ በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት ሊፈጽም ይችላል።

ማንም ሰው ጾታ ተኮር ጥቃት የደረሰበት ሊሆን ይችላል - ይህም በጋብቻ ያሉ ሰዎችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሰዎችን፣ አረጋውያንን ወይም በወሲብ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩት ጨምሮ ሌሎችንም ያጠቃላል።

ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ ማንነት እና ደኅንነት ይጠብቁ። ጥቃት ስለደረሰበት/ባት ግለሰብ ግላዊ/ገላጭ መረጃ ወይም ስላጋጠማቸው ጉዳት አለቃዎን ጨምሮ በቃል ለሌሎች ሰዎች አያጋሩ፣ ማስታወሻ አይፃፉ፣ ፎቶግራፍም አያንሱ። ጥቃት ስለደረሰበት/ባት ግለሰብ ድምጽ እየተቀዳ ነው የሚለውን ስጋት ለማስወገድ ስልኮትን እና ኮምፒውተሮትን አርቀው ያስቀምጡ።

- ግላዊ/ገላጭ መረጃ ጥቃት የደረሰበትን/ባት ግለሰብ ስም፣ የወንጀለኛውን ስም፣ የትውልድ ቀንን፣ የምዝገባ ቁጥርን፣ የመኖርያ አድራሻን፣ የሥራ ቦታ አድራሻን፣ ልጆቻቸው የሚማሩበት ትምህርት ቤትን ፣ ጥቃቱ የተከሰተበትን ትክክለኛ ሰዓት እና ቦታ ወዘተ ያካትታል።
- ጠቅለል ያለ እና ማንነትን የማይለይ መረጃ ያጋሩ፡
- የመርሐ ግብር ደኅንነት ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ለቡድንዎ ወይም ለሴክተር አጋሮችዎ ፡፡
- ለድጋፍ አውታረ መረብዎ ለራስ ለሚደረግ እክብካቤ እና ማበረታቻ በሚያስፈልግበት ወቅት፡፡

“ገለልተኛ እና ሩቅ ስለሆነ በውሃ መቅጃው አካባቢ ሰዎች ትንኮሳ እያጋጠማቸው እንደሆነ ተረድቻለሁ። ቅርብ የሆነን የውሃ ነጥብን መጠቀምን ወይንም በቡድን ሆኖ ውሃ መቅዳትን በማበረታታት ይህንን ትንኮሳ ለመቀነስ መሞከር እንችላለን ወይም…”

“አንድ ሰው በራሱ/ራሷ ላይ ስለደረሰ መጥፎ ነገር አጋርቶኛል/ታኛለች። ዝርዝሩን ማካፈል አልችልም፤ ግን ይህ መስተጋብር በእኔ ላይ ምን ተጽዕኖ እያሳደረብኝ እንደሆነ ለማወቅ ድጋፍ እፈልጋለሁ።

በጾታ ላይ የተ
ጥቃት የዳረ
ባትን/ ግለሰ
ጋር ብትመ
ማድረግ አለ

መሠረተ
ሰበት/
ብ እኔ
ገ ምን
ብኝ?

የውሳኔ ዛፍ

ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ክስተት ለእርስዎ ተነግሯል...

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ

ይመልከቱ እንዲሁም ያዳምጡ
(ገጽ 7 እና 8 ን ይመልከቱ)።

ራስዎን ያስተዋውቁ፡፡
እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ይጠይቁ።
አክብሮትን፣ ደህንነትን፣ ምስጥራዊነት እና አድልዎ ያለማድረግን ተግባራዊ ያድርጉ።

በሌላ ሰው...

ጥቃት ለደረሰበት/ባት ግለሰብ የሚሆን ማንኛውም አገልግሎት እና ድጋፍ ካለ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃን ያቅርቡ። ግለሰቡ ፈቃደኛ ሆኖ ሃሳቡን እንዲገልጽ ይህን መረጃ ደሳንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እና በምስጢር ጥቃት ከደረሰበት/ባት ግለሰብ ጋር መረጃ እንዲያጋራ እንዲያሳውቅ ያበረታቱ።

ማስታወሻ
ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የደረሰባቸውን ግለሰቦች አይፈልጉ፡፡

መዘጋጀት ስለሚገኙ አገልግሎቶች ግንዛቤ ይኑሮት።

ለህጻናት
እና በጉርምስና
እድሜ ለሚገኙ
ታዳጊዎች፣
ወደዚህ ገጽ ይሂዱ
17

በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት (GBV) ነው። ተዋናይ/የቅብብሎሽ መንገድ ይገኛል?

አዎ

ጥቃት ለደረሰበት/ባት ግለሰብ ጾታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች አገልግሎቶች ለማሳወቅ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የቅብብሎሽ መንገድን ይከተሉ እንዲሁም ከግለሰቡ/ቧ ፈቃድ ካገኙ ሪፈር ያድርጉ።

አይ

መስፈንጠርያ
(ገጽ 9 እና 10ን ይመልከቱ

ስለሚገኙ አገልግሎቶች ትክክለኛ መረጃን ያስተላልፉ።

ጥቃት የደረሰበትን/ባት ግለሰብ ከአገልግሎት ጋር ለመገናኘት ይመርጣልን?

አዎ

ዝርዝር መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፣ አስፈላጊ ጊዜዎችን እና ቦታዎችን፣ በአገልግሎቱ የትኩረት ነጥቦችን፣ ደኅንነቱ በተጠበቀ የመጓጓዣ አማራጮች ወዘተ. ላይ ስለሚገኙ መርጃዎች/አገልግሎቶች ግንኙነት ያድርጉ። ግልጽ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፈቃደኝነት ከሌለ በስተቀር ጥቃት ስለደረሰበት/ባት ግለሰብ ምንም አይነት መረጃ አያጋሩ። የክስተቱን ዝርዝሮች ወይም ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ መለያዎች አይመዝግቡ።

አይ

ምስጥራዊነትን ይጠብቁ።
ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ሀሳብ መቀየር እንደሚችል/እንደምትችል እና አግልግሎቱን ማግኘት እደሚችል/እንደምትችል ያስረዱ። አገልግሎቶች ጊዜያዊ፣ ተንቀሳቃሽ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚገኙ ከሆነ እነዚህ አገልግሎቶችን መስጠት መቼ እንደሚቆም መረጃ ይስጡ።

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ለእርዳታ በጠየቀው/ቺው መሰረት ለግለሰቡ/ቧ የምንገልጻቸው አግባብነት ያላቸው የድጋፍ አገልግሎቶች እነማን ናቸው?

የመረጃ ወረቀት

በአካባቢዎ ለሚገኙ አገልግሎቶች ይህንን የመረጃ ወረቀት ይሙሉ እና በቀላሉ ተደራሽ በሆነበት ቦታ ያኑሩ። አገልግሎቶች ሞዳሊቲያቸውን ሊለውጡ (ለምሳሌ ወደ ሩቅ ቦታ ወይም ተንቀሳቃሽ አገልግሎቶችን ወደመስጠት መሸጋገር)፣ አዲስ አገልግሎቶች ሊጀምሩ ወይም አገልግሎቶች ሊጠናቀቁ ስለሚችሉ ይህንን ወረቀት በየጊዜው ያሻሽሉ።

የሚከተሉትን ለመለየት ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ባለሙያ፣ የቡድን መሪዎ እና አጋሮች ጋር በመሆን ይስሩ፡ - (1) በሰብአዊ አጋሮች የሚቀርቡ አገልግሎቶችን እና (2) በመንግስት የሚቀርቡ አገልግሎቶች (3) ማኅበረሰብ ተኮር አገልግሎቶች ለምሳሌ የሃይማኖት ቡድኖች፣/ማምለክያ ቦታዎች፣ በሴቶች የሚመሩ ቡድኖች፣ ወጣት ተኮር ቡድኖች፣ የአካል ጉዳተኞች ድርጅቶች ወዘተ።

እነዚያን አገልግሎቶች እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፣ የት መሄድ እንዳለባቸው፣ ማንን ማነጋገር እንዳለባቸው እና ማን ሊያገኛቸው/ ሊያገኛቸው እንደማይችል ጨምሮ (ለምሳሌ ሴቶች ብቻ፣ አስፈላጊ ሰነዶች፣ ወዘተ) ጨምሮ አስፈላጊ መረጃዎችን ይጻፉ።

የቀበሌ ወይም የወረዳ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

የህጻናት ጥበቃ

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

የአእምሮ ጤንነት/የሥነ-ልቦና ድጋፍ

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ጤና

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ወሲባዊ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

የአስገድዶ መድፈር ህክምናዊ አያያዝ

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ፖሊስ ጣቢያ በቀበሌ / በወረዳ ደረጃ

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕቃዎች / WASH incl. የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ኪቶች

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

መጠለያ (ለምሳሌ የሴቶች መጠለያ)

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

የህግ

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ምግብ እና የአመጋገብ ስርአት

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

በጉርምስና እድሜ ለሚገኙ ታዳጊዎች / ወጣቶች የቀረቡ አገልግሎቶች

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ለአካል ጉዳተኞች የቀረቡ አገልግሎቶች

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

ለ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሰዎች የቀረቡ አገልግሎቶች

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

በህጻናት ወይም በሴት ለሚመሩ ቤተሰቦች የቀረቡ አገልግሎቶች

መረጃ: ____________________

የትኩረት ነጥቦች: ____________________

ስልክ ቁጥር: ____________________

የድርጅትዎ ከወሲባዊ ጥቃት እና ብዝበዛ ጥበቃ የትኩረት ነጥብ

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

አፎኖር እና ኢኮኖሚያዊ

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

የሴቶች ቡድኖች

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

ሌላ 1:

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

ሌላ 2:

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

ክልላዊ አገልግሎቶች

እነዚህ አገልግሎቶች በብዙ የክልል ዋና ከተሞች ይገኛሉ። ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት የክልሉን የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮን ያነጋግሩ።

ሁሉም በአንድ ቦታ የሚገኝበት ማእከል

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

ክልላዊ የስልክ መስመር/የእገዛ መስመር ለ GBV ምላሽ

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

ብሔራዊ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ማሳወቂያ የስልክ መስመር

በብሔራዊ ደረጃ የስልክ መስመር

መረጃ: ______________________________

የትኩረት ነጥቦች: ______________________________

ስልክ ቁጥር: ______________________________

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጠባዬን እንዴት ማድረግ አለብኝ?

ቁልፍ መደረግ ያለባቸው እና የሌለባቸው ነገሮች ምንድናቸው?

መደረግ ያለባቸው ፣ መደረግ የሌለባቸው እና ምን መባል እንዳበት

ተመልከት

አድርግ

አድርግ ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ወደ እርሶ እንዲመጣ / እንድትመጣ ያድርጉ። ፍላጎታቸውን አዳምጥ ::

አድርግ በመጀመሪያ በማንኛውም መሰረታዊ አስቸኳይ ፍላጎቶች እንዴት ድጋፍ ማድረግ እንደሚችሉ ይጠይቁ። አንዳንድ ጥቃት የደረሰባቸው ግለሰቦች ወዲያውኑ የህክምና እንክብካቤ ወይም ልብስ ይፈልጉ ይሆናል::

አድርግ አሁን ባሉበት ቦታ ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ምቾት የሚሰማው / የሚሰማት ከሆነ ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ ይጠይቁ ::

አድርግጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ከሌላው ሰው ጋር አብሮ / ራ ከሆነች ስላጋጠመው / ማት ነገር በዛ ሰው ፊት ማውራትን ደሳንነቱ የተጠበቀ ነው ብለው አያስቡ።

አድርግውሃ እንደማቅረብን ፣ ገለል ያለ የመቀመጫ ቦታ እንደማዘጋጀትን ፣ ፊት ማበሻ ሶፍትን እደማቅረብን ወዘተ የመሰሉ ተግባራዊ ድጋፎችን ያድርጉ።

አድርግአቅምዎ በፈቀደ መጠን ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ እንዲተረጉምላቸው እና / ወይም ካስፈለገም እንዲደግፋቸው የሚፈልጉት ሰው ካለ ይጠይቁ።

አታድርግ

አታድርግ መጥፎ ፣ ምቾት የማይሰጥ ወይም ስህተት የሆነ ነገር አጋጥሞኛል ብሎ ያጠመውን ነገር ለመናገር የሚመጣን ሰው ችላ ማለት

እና / ወይም ጥቃት።

አታድርግ ጣልቃ በመግባት እና ግፊት በማድረግ ሰውን ለመርዳት መሞከር ::

አታድርግ ከመጠን በላይ ምላሽ መስጠት። ይረጋጉ።

አታድርግ ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ መረጃን ለማጋራት ምቾት ከሚሰጠው / ከሚሰጣት መጠን በላይ እንዲያጋራ / እንድታጋራ ግፊት ማድረግ። የክስተቱ ዝርዝር በማን ተፈጸመ የሚለው ለእርሶ የማዳመጥ ምላሽ እና መረጃ የማቀበል ሂደት ጠቃሚ እና ተገቢ አይደለም

በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ ::

አታድርግ ግለሰቧን / ቡን ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እንደተፈጸመባት / በት ፣ እንደተደፈረች / ረ ፣ እንደተመታች / ታ ወዘተ… መጠየቅ።

ምን ብሎ መናገር እንደሚገባ ምሳሌዎች…

“በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሥቃይ ውስጥ ያለሽ / ህ ትመስያለሽ / ህ ፣ ወደ ጤና ክሊኒክ መሄድ ትፈልጊያለሽ / ህ?”

“ይህ ቦታ ለአንቺ / ተ ተስማሚ ነው? ጥሩ ስሜት የሚስጥሽ / ህ / ሌላ ቦታ አለ? እዚህ ቦታ ውይይት ለማድረግ ምቾት ይሰማሻል / ሃል? “

“ውሃ መጠጣት ትፈልጊያለሽ / ህ? እባክህ / ሽ ለመቀመጥ ነፃነት ይሰማሽ / ህ። “

መደረግ ያለባቸው ፣ መደረግ የሌለባቸው እና ምን መባል እንዳለበት

አዳምጥ

አድርግ

አድርግ ማንኛውንም መረጃ በምስጢራዊነት ይያዙ። ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ የበለጠ ለማገዝ እርዳታ እና መመርያ ከፈለጉ ባለሙያ ወይም የሥራ ባልደረባን ለማውራት የግለሰቡን/ቧን ፈቃድ ይጠይቁ። ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ የግል ማንነት ሳያሳውቁ ያድርጉ።

አድርግ በምስጢራዊነቶ መጠን ዙርያ እንደየአውዱ ግምትዎን ይመጥኑ።2

አድርግ በእርስዎ ሚና ላይ የሚጠበቁ ነገሮችን ያቀናብሩ።

አድርግ ከሚናገሩት በላይ ያዳምጡ።

አድርግ አንዳንድ የመጽናኛ እና የድጋፍ መግለጫዎችን ይናገሩ፤ በእነሱ ላይ የደረሰው ነገር ጥፋታቸው እንዳልሆነ አስረግጠው ይናገሩ።

አታድርግ

አታድርግ ማንኛውንም ነገር መጻፍ፣ ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ ፎቶ ማንሳት፣ ውይይቱን በስልክዎ ወይም በሌላ መሣሪያዎ መቅዳት ወይም ሚዲያን ጨምሮ ለሌሎች አካላት መረጃ መስጠት።

አታድርግ ስለተፈጠረው ነገር ጥያቄ መጠየቅ። ይልቁንስ ያዳምጡ እንዲሁም ለመደገፍ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ይጠይቁ።

አታድርግ በግለሰቡ/ቧ ተሞክሮ እና በሌላ ሰው ላይ በሆነ ነገር መካከል ንፅፅሮችን ማድረግ። ሁኔታው ትልቅ ጉዳይ ወይም አስፈላጊ እንዳልሆነ አይግለጹ። አስፈላጊው ነገር ከጥቃት የተረፈው / ቸው ግለሰብ ስላጋጠመው / ማት ነገር የሚሰማው / የሚሰማት ስሜት ነው።

አታድርግ መጠራጠር ወይም መቃወም ያስታውሱ ድርሻዎ ያለፍርድ ማዳመጥ እና በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ መረጃ መስጠት ነው።

ምን ብሎ መናገር እንደሚገባ ምሳሌዎች...

“እንዴት ላግዝዎት እችላለሁ?”

አብረን የተነጋገርነው ነገር በሙሉ በእኛ መካከል ብቻ ምስጢር ሆኖ ይቀራል። ያለ እርስዎ ፈቃድ ስለጉዳዩ ለማንም አላጋራም። “

“በተቻለኝ መጠን እርስዎን ለማገዝ እሞክራለሁ ፤ ነገር ግን ባለሙያ አማካሪ አይደለሁም።

ለእርስዎ የሚቀርብ የድጋፍ አገልግሎት ላይ ያለኝን ማንኛውንም መረጃ ማጋራት እችላለሁ። “

“እባክዎን ሊያካፍሉኝ የሚፈልጉት ማንኛውም ነገር ካለ ያካፍሉኝ። ለእርስዎ በሚቀርበው የድጋፍ አገልግሎት ላይ መረጃ እንድሰጥዎ ስለደረስብዎት ነገር ለእኔ መናገር አያስፈልግዎትም። “

“ይህ በእርስዎ ላይ በመድረሱ አዝናለሁ።”

“የተፈጠረው ነገር የእርስዎ ጥፋት አይደለም።”

መስፈንጠርያዎች

አድርግ

አድርግ ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ የራሱን / የራሷን ውሳኔ የመወሰን መብቱን / መብቷን ያክብሩ።

አድርግ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከል ላይ ያተኮሩ ልዩ አገልግሎቶች ባይሆኑም እንኳን በቦታው ያሉ ሁሉም አገልግሎቶች ላይ መረጃን ያጋሩ።

አድርግ ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ አሁን ውሳኔ የመወሰን ግዴታ እንደሌለበት / ባት ፤ ሀሳብ መቀየር እደሚችል / እንደምትችል እንዲሁም አነዚህን አገልግሎቶች እና ተንከባካቢውን / ዋ ወይም እምነት የሚጥልበትን / የምትጥልበትን ማንኛውም ሰው ጋር ለእርዳታ መሄድ እደሚችል / እንደምትችል ይንገሩ።

አድርግ ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ የሚያምነውን / የምታምነውን ሰው ማግኘት እንዲችል / እንድትችል ደኅንነቱ የተጠበቀ ነው ብለው ካሰቡ ስልኮን ወይም የመገናኛ መሳርያዎን ያቅርቡ።

አድርግ ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ ፈቃድ ይጠይቁ።

አድርግ አበረታች በሆነ መንገድ ይቋጩ።

አታድርግ

አታድርግ ችሎታዎን ማጋነን ፤ የሐሰት ተስፋዎችን መስጠት ወይም የሐሰት መረጃን መስጠት ።

አታድርግ የራስዎን ምክር መስጠት ወይም ምን ድርጊት ቢወሰድ ወይም ቀጣይ እርምጃ ምን መሆን አለበት የሚለው ላይ አስተያየት መስጠት።

አታድርግ አንድ ሰው ምን እንደሚፈልግ ወይም እንደሚያስፈልገው አውቃለሁ ብሎ ማሰብ። አንዳንድ ድርጊቶች አንድን ሰው ለበለጠ መገለል ፤ በቀል እና ጉዳት ሊያጋልጡት ይችላሉ።

አታድርግ ስለ አንድ ሰው ወይም ስላጋጠማቸው ነገር ግምት መውሰድ እንዲሁም በማንኛውም ምክንያት ማለትም በእድሜ ፤ በጋብቻ ሁኔታ ፤ በአካል ጉዳተኝነት ፤ በሃይማኖት ፤ በብሔር ፤ በኑሮ ደረጃ ፤ በወሲባዊ ዝባሌ ፤ በጾታ ማንነት ፤ በጥቃት አድራሹ (ሾቹ) ማንነት ወዘተ በመመስረት አድልኦ ማድረግ

አታድርግ ሰላምን ለማድረግ ፤ ለማስታረቅ ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በደረሰበት / ባት ግለሰብ እና በሌላ ሰው (እንደ ጥቃት አድራሽ ፤ ወይም ሌላ ሶስተኛ ግለሰብ ለምሳሌ እንደ ቤተሰብ ፤ የማኅበረሰብ የኮሚቴ አባል ፤ ወይም የማኅበረሰብ መሪ ወዘተ.) መካከል ሁኔታውን ለመፍታት ይሞክሩ።

አታድርግ የተከሰተውን ጥቃት ዝርዝር መረጃ እና ጥቃት የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ የግል መለያዎች ማካፈል። ይህ የደረሰበትን/ባትን ግለሰብ የቤተሰብ አባላት ፤ የፖሊስ / የጸጥታ ኃይሎች ፤ የማኅበረሰብ መሪዎች ፤ የስራ ባልደረቦች ፤ ተቆጣጣሪዎች ፤ ወዘተ… ያካትታል። ይህንን መረጃ ማጋራት ጥቃት ለደረሰበት/ባት ግለሰብ የበለጠ ጉዳት ያስከትላል።

አታድርግ ውይይቱን ከጨረሱ በኋላ ከጥቃት ስለደረሰበትን/ባት ግለሰብ መጠየቅ ወይም ግለሰቡን / ቧን ማግኘት።

መስፈንጠርያዎች (የቀጠለ)

ምን ብሎ መናገር እንደሚገባ ምሳሌዎች...

"የተነጋገርነው ነገር በእኛ መካከል ይቀራል።"

"እኔ አማካሪ ባለሙያ አይደለሁም ፤ ነገር ግን ያለኝን መረጃ ላካፍልዎ እችላለሁ። ለእርስዎ እና / ወይም ለቤተሰብዎ መጠነኛ ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አንዳንድ ሰዎች / ወይም ድርጅቶች አሉ። ስለእነሱ ማወቅ ይፈልጋሉ? "

"የአገልግሎቱ ዝርዝር ማለትም ቦታውን ፣ አገልግሎቱ ክፍት የሚሆንባቸውን ጊዜያት ፣ ዋጋውን (ካለው) ፣ የመጓጓዣ አማራጮችን እና ማነጋገር የሚችሉትን ሰው ስም ጨምሮ እንደሚከተለው ያግኙ።"

"ድጋፍ ሊያደርግልዎ የሚችል እምነት የሚጥሉበት ሰው አለ? ምናልባት የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ? በዚህ ሰዓት በእኔ ስልክ ደውለው ሊጠሩት የምትፈልጉት ሰው አለ? "

"ቀጣዩ እርምጃዎትን በሚመለከት የሚፈልጉትን እና ምቾት የሚሰጥዎትን ነገር ከግምት ወስጥ ማስገባት በጣም አስፈላጊ ነው።"

"አሁኑኑ መወሰን አለብኝ የሚል የስሜት ጫና አይደርቦት። ስለጉዳዩ አሰላስለው ወደፊት በፈለጉበት ጊዜ ሀሳብዎን መለወጥ ይችላሉ። "

"ችግሩን ለመፍታት በእርስዎ ስም ከማንም ጋር መወያየት አልችልም። ነገር ግን እኔ ማድረግ የምችለው በውይይታችን ወቅት ለእርስዎ ድጋፍ መስጠት እና የሚያሳስቦትን ነገር ማዳመጥ ነው። "

"ከዚህ በኋላ እንዴት መጓዝ እንደሚፈልጉ ዕቅድ ያለዎት ይመስላል። ያ መልካም እርምጃ ነው። "

"ከዚህ በኋላ እንዴት መጓዝ እንደሚፈልጉ ዕቅድ ያለዎት ይመስላል። ያ መልካም እርምጃ ነው። "

ደረጃ

መ

ዘርዘ

መጀመ

በደረጃ እንዴት
ቀጠል አለብኝ
ር መመርያዎች
ምንድናቸው
ከሥነ-ልቦና
መርያ እርዳታ ጋር
የተገናኙት?

ዝርዝር መመሪያ
ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ምልከታ፡
ድጋፍ የመፈለግ ጥቅሞች እና አደጋዎች

አገልግሎቶችን መፈለግ ጥቃት ለደረሰበት/ባት ግለሰብ ሁልጊዜ ደህንነቱ የተጠበቀ አይደለም እናም የበለጠ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። የእርስዎ ሚና በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃን ማቅረብ እና ጥቃት ለደረሰበት/ባት ግለሰብ ግለሰብ ደህንነት በሚሰማው / ማት መልኩ የራሱን / ሷን ምርጫ እንዲያደርግ / እንድታደርግ ማስቻል መሆኑን ያስታውሱ። የሚከተለውን የጥቅሞች ወይም የአደጋዎች ምሳሌ ይመልከቱ፡

ድጋፍ የመፈለግ አደጋዎች

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ጓደኞች ፣ ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ ክስተቱን ሲያውቁ የመገለል ፣ ከቤት ወይም ከማኅበረሰቡ የመባረር እና / ወይም ለተጨማሪ ጥቃት የመጋለጥ እድል ሊኖረው / ራት ይችላል።፡

ጥቃት ፈጻሚ (ዎች) የተፈጠረውን ነገር ሌሎች እንደሰሙ ካወቁ ጥቃት የደረሰበትን ሰው እስከ መጉዳት ወይም እስከ መግደል ድረስ ወደ በቀል ሊያመሩ ይችላሉ።

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብን ሲረዱ ከታዩ አገልግሎት ሰጪዎች በጥቃት አድራጊዎች ወይም በማኅበረሰቡ ለዛቻ እና ለጥቃት ሊዳረጉ ይችላሉ።

አገልግሎት አቅራቢዎች በተገቢው መንገድ ካልሰለጠኑ ከመጠን በላይ የሆነ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ።

ድጋፍ የመፈለግ ጥቅሞች

በአደጋ ጊዜ ሕይወት አድን ድጋፍ ተደራሽነት።

ኤች. አይ. ቪን እና ያልተፈለገ እርግዝናን ለመከላከል የሚያስችል ወቅታዊ ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ ምስጥራዊ እና ሙያዊ የህክምና አገልግሎት ተደራሽነት

የደህንነት እና የስነ-ልቦና ድጋፍ የሚሰጡ አማራጮችን ጨምሮ የበለጠ ክብር እና ምቾት የሚሰጡ የሌሎች አገልግሎቶች ተደራሽነት።

ያንን የመደገፍ ተደራሽነት ተጨማሪ ጥቃት እንዳይከሰት ሊከላከል ይችላል ።

ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት
በሰብአዊ ተዋናይ ወይም ከሰብአዊ ድጋፍ ጋር የተገናኘ ግለሰብ

የጾታዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ (PSEA) ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን በሰብአዊ ሥራ ላይ በተሰማሩ ሰራተኞች ወይም ተያያዥነት ባላቸው ባለሙያዎች ማለትም በሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞች፣ በበጎ ፈቃደኞች፣ በጥበቃ ሠራተኞች ፣ በሥራ ተቋራጮች ፣ በአሽከርካሪዎች ፣ በተባበሩት መንግስታት ተልዕኮ ላይ በሚሳተፉ ግለሰቦች፣ በሰላም አስከባሪዎች፣ ለሰብአዊ ጉዳዮች ሸቀጦችና አገልግሎት በሚያቀርቡ አካላት ከሚፈጸሙ ጾታዊ ብዝበዛ እና ጥቃቶች ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎችን ለማመልከት የሚያገለግል ቃል ነው።

ወንጀለኛው ማንም ይሁን ማን በዚህ መርጃ ላይ እንደተመለከተው ከታ ተኮር ጥቃት (GBV) የደረሰበት/ባትን ግለሰብ ለመደገፍ ፍኖተ ካርታው ተመሳሳይ ነው። ወንጀለኛው የእርዳታ ሠራተኛ ወይም ከሰብዓዊ እርዳታ ጋር የተቆራኘ በሚሆንበት ጊዜ ለሚነሱ ተጨማሪ ኃላፊነቶች ፣ የወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል (PSEA) ማእከልን ወይም በአገር ውስጥ ያለን የወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል አውታረ መረብን ያግኙ።

ተዘጋጅ

መዘጋጀት ቁልፍ ነው።

በአካባቢዎ የጾታ ተኮር ጥቃት ተዋናይ (የጾታ ተኮር ጥቃት ሪፈራል ወይም የትኩረት ነጥብን ጨምሮ) ባይኖርም ፣ የአንድን ሰው ፍላጎት ለማርካት የሚረዱ በአከባቢ / በማኅበረሰብ ደረጃ ያሉትን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ምናልባት እርስዎ ከሚያስቡት በላይ ስለ ብዙ አገልግሎቶች ያውቁ ይሆናል!

ምናልባት እርስዎ ከሚያስቡት በላይ ስለ ብዙ አገልግሎቶች ያውቁ ይሆናል!

ስለሚገኙ አገልግሎቶች መረጃ ለመሙላት የመረጃውን ሰነድ (ገጽ 5 እና 6) ይጠቀሙ። ጾታን መሰረት ያደረጋ ጥቃት (GBV) ባለሙያ ፣ ከቡድን መሪዎ ፣ ከሥራ ባልደረቦችዎ እና ከሌሎች አጋሮችዎ ጋር ይሥሩ።

እነዚያን አገልግሎቶች እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ማለትም ወደ የት መሄድ ፣ ማንን ማነጋገር እና ማንን ማግኘት እንደሚገባ ማን ሊያገኛቸው / ሊያገኛቸው እንደማይችል ጨምሮ አስፈላጊ መረጃዎችን ይፃፉ (ለምሳሌ ሴቶች ብቻ ፣ አስፈላጊ ሰነዶች ፣ ወዘተ ...)።

ወሲባዊ ብዝበዛን እና ጥቃትን ስለመከላከል ፕሮቶኮሎች የቡድን መሪዎን ፣ የፕሮግራም ሥራ አስኪያጅዎን እና / ወይም የክላስተር / የዘርፉን አስተባባሪ ይጠይቁ። ወኪልዎ ለወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ የተቋቋመ ፕሮቶኮል ከሌለው በቅንብርዎ ውስጥ መመሪያ ለማግኘት ወደ ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት ጥበቃ የትኩረት ነጥብ ለመድረስ ያስቡበት።

ልምምድ ፍጹም ያደርጋል

ከገጽ 7-10 ባሉት የናሙና ጽሁፎች በደንብ ይለማዱ። አብረው ከሚሰሩት ሰው ጋር ወይም ከጓደኞች ጋር በደንብ ይለማመዱ ። ብዙ በተለማመዱ መጠን ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት (GBV) የደረሰበት ሰው የእርሶን እርዳታ ሲፈልግ አይቸገሩም።

በእነዚህ ቁሳቁሶች ላይ እንዴት ማሠልጠን / መለማመድ እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የተጠቃሚ ምክሮች መመሪያን (User Tips Manual) ይመልከቱ።

የኪስ መመሪያው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚያልፍ ማንኛውም ሰው ጠቃሚ ነው። በሚቀጥለው ጊዜ የሥራ ባልደረባዎ ወይም ጓደኛዎ ድጋፍ ወይም ምክር ለማግኘት ወደ እርስዎ በሚመጣበት / በምትመጣበት ጊዜ በዚህ መርጃ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች እና መግለጫዎች በመጠቀም ይለማመዱ።

ተመልከት

አንድ / ዷት ግለሰብ በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት እንደደረሰበት / ባት ለእርስዎ ቢገልጽልዎት / ብትገልጽልዎት ...

ራስዎን ያስተዋውቁ

ስምዎን ፣ ሚናዎን እና ማንነትዎን ያስተዋውቁ። እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ይጠይቁ።

ለአስቸኳይ መሠረታዊ ፍላጎቶችን መፍትሔ ይስጡ።

እያንዳንዱ ሰው የተለያዩ መሰረታዊ ፍላጎቶች ይኖረዋል ፤ ይህም አስቸኳይ የህክምና ክብካቤን ፣ ውሃን ፣ የሚወዱትን ሰው መፈለግን ወይም ብርድ ልብስን ወይም ልብስ ከጠፉ ፣ ከተቀደደ ፣ ከቆሸሸ ወይም ከተወገደን ይጨምራል። በተለይም የደረሰባቸው ግለሰቦች የበለጠ ምቾት እና ክብር እንዲሰማቸው ለማድረግ ዋናው አስቸኳይ ፍላጎት አልባሳት ሊሆኑ ይችላሉ።

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ስለ ግል ደህንነቱ ይንገርዎት / ትንገርዎት። በሚያዩት ነገር ላይ በመመርኮዝ ግምቶችን ላለማድረግ ይጠንቀቁ።

ሰዎች ድጋፍ ለመሻት የተለያዩ መንገዶች እንደሚጠቀሙ ልብ ይበሉ

ሰዎች ስሜታቸውን በተመቻቸው መልኩ እንዲገልጹ ይፍቀዱላቸው። ሰዎች ለጭንቀት እና ለቀውስ የተለያዩ ዓይነት ምላሾች አሏቸው። አንዳንድ ሰዎች ዝምተኛ እና መናገር የማይችሉ፣ ተቆጪ እና ኃይለ ቃል የሚናገሩ፣ በደረሰባቸው ነገር ላይ እራሳቸውን ተጠያቂ የሚያደርጉ፣የሚያለቅሱ፣ጠበኛ ወዘተ...ሊሆኑ ይችላሉ።

ተመልከት (የቀጠለ)

የአካል ጉዳት ያለባቸው ፣ የተለየ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ እና ሌሎች ሰዎች ድጋፍ ለማግኘት ሲፈልጉ የተለያዩ እንቅፋቶች ያጋጥሟቸዋል። ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ያማከለ ይሁን

እነዚህን ሰዎች ለማዳመጥ እና የሚረዱበትን መንገድ ለማወቅ ሲፈልጉ መርህ እና ምስጢራዊነትን ይከተሉ። አንድን ሰው መረዳት ባይችሉ እንኳ ሁል ጊዜ ክብካቤ እና ድጋፍን ማሳየት ይችላሉ።

በተለይም አዋቂ ሴቶች እና/ወይም ሴት ልጆች ከወንዶች ጋር መግባባት የማይችሉበት ባህላዊ ሁኔታ ካለ ሴት ሠራተኞች ድጋፍ ለመስጠት መገኘታቸውን ማረጋገጥ።

ምን ማስተዳደር እንደሚችሉ እና እንደማይችሉ ይገንዘቡ

አንዳንድ ሁኔታዎች ከእርስዎ ሚና ባሻገር የበለጠ ልዩ የባለሙያ ድጋፍ ይፈልጋሉ ፤ ለምሳሌ ህጻናትን ያካተቱ ሁኔታዎች፣ አስገዳጅ ሪፖርት አደራረግ፣ [3]ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ላይ የማይቀር አደጋ፣ ወይም ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ በራሷ/በራሱ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት የምታደርስበት/የሚያደርስበት ሁኔታዎች። ሌሎች የትኩረት ነጥቦች ሊኖሩ ይችላሉ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተሻለ ድጋፍ ለመስጠት አቅም ያላቸው፡፡ የመረጃ ሰነድዎን ይመልከቱ

(ገጽ 5 እና 6)፡፡

ያስታውሱ ፣ ከተቆጣጣሪ ወይም ከሌላ የሰብዓዊ ባለሙያ ድጋፍ መጠየቅ ከፈለጉ ፣ ሁልጊዜም በቅድሚያ ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ ፈቃድ ይጠይቁ።

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ማንን ማነጋገር እንደሚፈልጉ ፣ ለምን ከእርሷ/ሱ ጋር መነጋገር እንደፈለጉ እና ምን አይነት መረጃ ለማጋራት እንደሚፈልጉ ይንገሩ። ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ጥሩ ስሜት ካልተሰማት/ው ወይም ሙሉ በሙሉ መረጃዎቸን ለማካፈል ፈቃደኛ ካልሆነች/ነ፣ በዚህ በኪስ የሚያዝ መመሪያ ውስጥ ያሉትን መሳሪያዎች በመጠቀም በተቻለ መጠን እርዳታ ያድርጉ።

3 ከአንዳንድ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ አስገዳጅ የሪፖርት ማድረግያ ሕጎችን የያዙ አንዳንድ አውዶች አሉ። ለተጨማሪ መረጃ እና መመሪያ የጥበቃ የትኩረት ነጥብዎን እና / ወይም ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ባለሙያን ያጣቅሱ።

አዳምጥ

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በቅርበት ሊከሰት የሚችል አደጋ ውስጥ አለመሆኑን/ኗን ማረጋገጥ ያዳምጡ።

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ የተበሳጨ/ች እና/ወይም ግራ የተጋባ/ች ይችላል/ትችላለች፣ ግን እንደ ድጋፍ ሰጪ በተቻለ መጠን ተረጋግቶ መኖር መቆየት ጠቃሚ ነው። ግለሰቡ/ቧ የሚፈልገውን/ምትፈልገውን ያህል ወይም ትንሽ መረጃ እንዲያጋራ/እንድታጋራ ይፍቀዱ። የምክር አገልግሎት መስጠት ፣ ግለሰቡን ወደ አገልግሎቶች መውሰድ ወይም

ስለደረሰው ነገር ዝርዝር ቃለመጠይቅ ማድረግ የእርስዎ ድርሻ አይደለም። ስለ ክስተቱ ዝርዝር ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ይልቅ ስለሚያውቋቸው አገልግሎቶች መረጃ መስጠት ላይ ያተኩሩ።

ጠቃሚ ምክር: በተለይም በ“ለምን?” የሚጀምሩ ጥያቄዎችን ማስወገድ በጣም ጥሩ ነው፣ ምክንያቱም እንደዚህ ያሉት ጥያቄዎች ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ላይ የጥፋተኝነት ስሜት ያሳድራል፡፡ ይልቁንስ ዝም ብለው ያዳምጡ ወይም አስፈላጊ ከሆነ

"እንተን/ቺን ለመደገፍ ስለሚገኙ አገልግሎቶች ልነግርህ/ሽ እችላለሁ” ወይም "እንዴት እንድደግፍዎት ይፈልጋሉ?" የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

የማዳመጥ ኃይል:

አንዳንድ ጊዜ እርስዎ ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ሊያጋሩት የሚችሉት የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም ሀብቶች መረጃ በፍጹም በማይገኙበት ሁኔታ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ። የተስፋ ቢስነት ስሜት ሊሰማዎት ይችላል። ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ የደረሰውን ነገር ለእርስዎ ለማካፈል ያሳዩትን ድፍረት በማድነቅ

በውይይታችሁ ሂደት ወቅት ሐቀኛ መሆንዎ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ለግለሰቧ/ቡ ትልቅ ክብር በመስጠት እርስዎ የበለጠ ሊያግዟቸው ባለመቻልዎ ማዘንዎን መግለፅ በጣም አስፈላጊ ነው። በአካል መገኘት በንቃት እያዳመጡ መሆኑን ለማሳየት በራሱ ትልቅ ድጋፍ ነው ፤ ድጋፍንም ማሳያ ነው።

በራሱ

መስፈንጠርያዎች

በሚቀጥሉት እርምጃዎች ላይ ውሳኔ እንዲያደርጉ ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ ሲደግፉ...

ጥቃት የደረሰባት/በትን ግለሰብ ለድጋፍ የምትሄድበት/የሚሄድበት እና የምትተማመንበት/ሚተማመንበት ሰው ካለ ይጠይቁ።

የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው ተብሎ ከተጠየቀ ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብን ወደ ማን፣ መቼ እና ለምን መሄድ እንዳለበት ውሳኔዎችን እንዲያደርግ ያበረታቱ።

ስለሁኔታው የራስዎን አስተያየት አይስጡ።

ማናቸውም አገልግሎቶች ወይም የበለጠ ምቾት ለማግኘት አማራጮች ካሉ በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ ትክክለኛውን መረጃ ጥቃት ለደረሰበት/ባት ግለሰብ ያቅርቡ።

ዝግጅት ቁልፍ ነው። የመረጃ ሰነድዎን (ገጽ 5 እና 6) ይጠቀሙ እና በሚገኙት አገልግሎቶች እና እነሱን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ትክክለኛ ፣ ወቅታዊ መረጃ እንዳለዎት ያረጋግጡ ።

አንድ የተወሰነ አገልግሎት መኖሩን እርግጠኛ ካልሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም ይበሉ።

ውይይቱን በርህራሄ ይጨርሱ።

ምስጥራዊነትን ይጠብቁ።

ጥቃት የደረሰበት/ባት ግለሰብ የሚያደርገውን/የምታደርገውን ውሳኔ በአዎንታዊ መልኩ ማጠናከር።

ሚናዎ ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ በውሳኔው/ዋ እና በምርጫው/ዋ መደገፍ ነው። ምንም እንኳን ግለሰቡ/ቧ ውሳኔም ምርጫም ባይኖረውም/ባይኖራትም። ጥቃት ከደረሰበት/ባት ግለሰብ ጋር ተደጋጋሚ ቆይታዎችን፣ ስብሰባዎችን፣ የማማከር አገልግሎትን ወይም የግለሰቡን ጉዳይን ለማስተዳደር ሙከራ አያድርጉ።

ከውይይቱ በኋላ

ማንፀባረቅ እና ራስን መንከባከብ: ሁሉንም ነገር በትክክል ማከናወን እንደሚችሉ ማስታወሱ አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን የዚህን ሰው ተሞክሮ ለማስተካከል ወይም ህመማቸውን ለማስወገድ አይችሉም። የሌሎች ሰዎችን ልምዶች ማዳመጥ እና መስማት ለስቃያቸው ፣ ለስሜት ቀውሳቸው ወይም ለጉዳት ልምዳቸው ሊያጋልጥዎ ይችላል - ይህም ሁለተኛ ደረጃ የስሜት ቀውስ በመባል ይታወቃል። እነዚህ ስሜቶች ከእርስዎ ሲወጡ እራስዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ያስቡ። የልውውጡን አጭር መግለጫ በተመለከተ (ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ መረጃ ምስጢራዊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት) የሥራ ባልደረቦችዎን ፣ የቡድን መሪዎን ወይም የጾታ ተኮር ጥቃት ስፔሻሊስትዎን ጨምሮ ለራስዎ የድጋፍ ስርዓት እና አውታረ መረብ ያግኙ እና ድጋፍ ይፈልጉ።

የተወሰኑ የጥቃት ዓይነቶች (ለምሳሌ የቤት ውስጥ ጥቃቶች) በተደጋጋሚ ሊከሰቱ ስለሚችሉ፣ ግለሰቡን/ቧን እንደገና ሊያዩት/ሊያዩዋት ወይም ሌላ የጥቃት ክስተት እንደገጠመው/ማት ሊያውቁ ይችላሉ። የደረሰባቸውን ነገር ሊለውጡት አይችሉም ነገር ነገር ግን እነዚህን ማድረግ ይችላሉ፦

ጥቃት የደረሰበት/ባትን ግለሰብ ከዚህ ቀደም አናግረውም ቢሆን በየአንዳንዱ የጥቃት ክስተት ፍርድ ሳይሰጡ ያዳምጡ።

ፕሮግራምዎን እንዴት እንደሚያሻሽሉ ያስቡ፣ የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ለማድረግ እና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት (GBV) ለደረሰባቸው ሰዎች የበለጠ አዎንታዊ አካባቢን ለመፍጠር ያስቡ።

ምናልባት ወደ እኔ የመጣው/ የመጣችው ህጻን ወይም ጎርምስና እድሜ ያለ/ያለች ልጅ ከሆነስ/ ከሆነችስ?

ከ 18 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት እና በጉርምስና እድሜ ላሉ ልጆች ድጋፍ መስጠት

ቁልፍ መልዕክቶች

ሁል ጊዜ በሀገርዎ/በአውድዎ ውስጥ ጾታን መሰረት ላደረገ ጥቃት ወይም ለህጻናት ጥበቃ ባለሙያ በመጀመሪያ (1) በአካባቢዎ ምን ዓይነት አገልግሎቶች እንደሚገኙ እና (2) አካባቢያዊ ፕሮቶኮሎች እና አሠራሮችን ለመረዳት እርሱን/እርሷ ያናግሩ።4

ጉዳት አያድርሱ፡፡ ጥቃት የደረሰባቸውን ህጻናትን አይፈልጉ። አንድን ህጻን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለን/ያለችን ልጅ ጥቃት እየደረሰበት/እየደረሰባት መሆኑን መመርመር ወይም መገምገም የእርስዎ ሥራ አይደለም፡፡

ይህን ማድረግ ህጻኑ/ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው/ያለችው ልጅ ለበለጠ አመፅ እና አደጋ እንዲጋለጥ/እንድትጋለጥ ያደርጋል።

ይህን ማድረግ ህጻኑ/ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው/ያለችው ልጅ ለበለጠ አመፅ እና አደጋ እንዲጋለጥ/እንድትጋለጥ ያደርጋል።

ሚናዎን ያስታውሱ አንድ/ዷት ህጻን /

በጉርምስና እድሜ ያለ/ያለች ልጅ ለእርዳታ ወደ እርሶዎ ከደረሰ/ች፣

1. ከፍርድ ነፃ የሆነ የሚያዳምጥ ጆሮ ያቅርቡ።
2. ህጻኗን/ኑን በጉርምስና እድሜ ያለችውን/ያለውን ልጅ ለደህንነቷ/ቱ ስጋት የማትጥልበት/የማይጥልበት እና እምነት የሚጣልባት/በት ብላ/ሎ ከለየው አዋቂ ግለሰብ ጋር በማገናኘት ይደግፉ። ግለሰቧ/ቡ ምናልባት የእሷ/ሱ ወላጅ፣ ተንከባካቢ ወይም የቤተሰብ አባል ላይሆን ይችላል፡፡
3. ከእሱ/እሷ ጋር በሚያወሩ ሰዓት የህጻኑን/ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለውን/ያለችውን ልጅ ተንከባካቢንም ሆነ ሌላ ሰውን ማስገደድ ጨምሮ በእሱ/እሷ ቦታ ሆነው ውሳኔዎችን አይወስኑ።

ማጽናኛ ይስጡ፡፡ ምንም እንኳን አብረው ሆነው በዝምታ መቆየት ቢኖርብዎትም ህፃኗ/ፃኑ /በጉርምስና እድሜ ያለችው/ው ልጅ ውይይቱን እንድትመራ/እንዲመራ ይፍቀዱ፡፡ ህፃኗ/ፃኑ /በጉርምስና እድሜ ያለችው/ው ልጅ በግልጽ ከእርስዎ ጋር መነጋገር እንደሚችሉ ለማሳየት ሰውነትዎን ዘና እድርገው ዓይን ለዓይን በምትተያዩበት ከፍታ ይሁኑ።

የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነ፡፡ ስለተከሰተው ነገር በማን እና ለምን የሚሉትን ጥያቄዎች ከመጠየቅ ይቆጠቡ - ይልቁንስ የሚያጽናኑ ቃላትን እና ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም በሚገባቸው መንገድ ይናገሩ።

ያስታውሱ በአካባቢዎ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ወይም የህጻናት ጥበቃ ተዋናይ/ቅብብሎሽ መንገድ የሚገኝ ከሆነ የህጻኑን/ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለውን/ያለችውን ልጅ ይበልጥ ለመርዳት ደህንነቱ እና ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ መልኩ ወደ ልዩ ባለሙያተኛ ሪፈራል ያመቻቹ። ይህንን መመሪያ **ጾታን መሰረት ያደረገን ጥቃት ወይም ህጻናትን ከጥቃት የመጠበቅ ስራን የሚሰራ/የቅብብሎሽ መንገድ** በአካባቢዎ በማይኖርበት ጊዜ ይጠቀሙ።

የሚከተሉትን ጨምሮ በአካባቢያዊ ፕሮቶኮሎች እና አሰራር ቅደም ተከተሎች ላይ የGBV ወይም በሀገር ውስጥ ያለ የህጻናት ደሳንነት ጥበቃን ያጣቅሱ፡ 1) በምስጢራዊነት ገደብ ላይ እና 2) የተሰየመ የGBV እና የህጻናት ደሳንነት ጥበቃ የትኩረት ነጥቦች

ሁሉንም ህጻናት በፍትሃዊነት ይዩ።

ጾታቸው እና እድሜአቸው ምንም ይሁን ሁሉም ልጆች አንድ አይነት የማያዳላ ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል

ወይም ሌላ የማንነታቸው መገለጫ ምንም ይሁን ምን ሁሉም ህጻናት አንድ ዓይነት ከመድልዎ የፀዳ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት (GBV) ያጋጠማትን/መውን ህጻን ተስፋ እንደሌላት/ለው አድርገው አያስተናግዱ። እያንዳንዱ ህጻን ልዩ ችሎታ እና ጥንካሬ አለው እንዲሁም የመፈወስ አቅም አለው/ላት፡፡ ጥቃት የደረሰባት/በት ን ህጻን በሚያናግሩበት ጊዜ በሚገባት/ው እና ለክብሯ/ሩ እና ለአስተያየቷ/ቱ አክብሮት በሰጠ መንገድ ይሁን።

ምስጥራዊነትን ይጠብቁ።

ከህጻኑ/ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ካለው/ካለችው ልጅ ጋር በሚኖርዎት ግንኙነት በምንም መንገድ ማስታወሻ አይፃፉ፣ ፎቶዎችን ወይም ሰነዶችን አይውሰዱ። ውይይቱን እየቀረጹ እንደሆነ ሊያመላክቱ የሚችሉ ማናቸውንም ስልኮች ወይም ኮምፒውተሮች አርቀው ያስቀምጡ። ስለ ህጻኑ/ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው/ያለችው ልጅ ወይም ስላጋጠማቸው ነገር ማንኛውንም መረጃ ለማጋራት ፈቃድ ይጠይቁ። ይህ ማለት ህጻኑ/ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው/ያለችው ልጅ ለሚተማመንበት/ምትተማመንበት ሰው እንኳን መረጃውን ማጋራት ይችሉ እንደሆነ መጠየቅ ነው።

የህጻኑን ደህንነት ያረጋግጡ::

የህጻኑ/ኗ አካላዊ እና ስሜታዊ ደህንነት ዋነኛው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ከእሱ ወይም ከእሷ ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ እና ከሚቀጥሉት ማናቸውም እርምጃዎች ጋር በተያያዘ የህጻኑ/ኗን ደህንነት ያስቡ።

በአንዳንድ ሁኔታዎች **ለህጻኑ ምርጥ ፍላጎት** እና ለእሱ/እሷ አካላዊ እና አእምሯዊ ደህንነት እንዴት ድጋፍ መስጠት እንደሚቻል ግልጽ ላይሆን ይችላል:: ስለ ሁኔታው ደኅንነት እርግጠኛ ካልሆኑ ደህንነቷ/ቱን ለማረጋገጥ የበለጠ እውቀት ያለውን ሌላ አገልግሎት ሰጪ ወይም የቡድን አባልን በምስጢር ማነጋገር እንደሚያስፈልግ ለልጁ/ቷ ያሳውቁ::

አንድ ህጻን/በጉርምስና እድሜ ያለ/ች ወንድ/ሴት ልጅ ወይም አሳዳጊያቻቸው እንዴት ድጋፍ ሊፈልጉ እንደሚችሉ ይወቁ።

ህጻናት እና በጉርምስና እድሜ ያሉ ልጆች ከአዋቂዎች በተለየ መንገድ እርዳታ ይፈልጋሉ፤ በአብዛኛውም ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን አይገልጹም። ህጻናት አዋቂዎችን በተለይም በደንብ የማያውቋቸውን አዋቂዎችን ማመን ወይም ማውራት ሊከብዳቸው፣ ፍርሃት ሊያድርባቸው፣ መሸማቀቅ ወይም ሀፍረት ሊሰማቸው፣ ወይም ስሜታቸውን ለመግለጽ ፍራቻ ሊታይባቸው ይችላል። በመሆኑም የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ-(1) በልጆች ላይ ስለሚፈጸሙ በደሎች የሚነገሩ ጭምጭምታዎችን መስማት፣ (2) ለአንድ ህጻን እርዳታ ፈልገው የሚመጡ አዋቂዎችን መቅረብ ወይም (3) ህጻኗ/ኑ ከምታሳየው/ከሚያሳየው ጠባዮች በመነሳት ጥቃት ይኑር ወይ አይኑር መገመት።

መደረግ ያለባቸው እና መደረግ የሌለባቸው

አንድ ሰው እርዳታ ስለሚያስፈልገው ህጻን ወይም በጉርምስና እድሜ ስላለ ልጅ ድጋፍ ከጠየቀ...

አድርግ ድጋፍ ለጠየቀዎት ግለሰብ በሚገኙ አገልግሎቶች ላይ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃዎችን ያቅርቡ።

አድርግ ምስጢራዊነትን መጠበቅ።4

አታድርግ አንድን አሉባልታ መመርመር ወይም ህጻኑን/ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው/ያለቸው ልጅን ለማግኘት/ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ መፈለግ።

አታድርግ ያወቁትን ነገሮች ዝርዝር ነገር ከማንኛውም ሰው ጋር መወያየት ወይም መነጋር።4

ተመልከት

ህጻኑ/ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው/ያለቸው ልጅ የእርሶን እርዳታ ከፈለገ/ቸ...

አድርግ ለመናገር ጸጥታ ያለው እና ገለል ያለ ቦታ ማግኘት ከፈለጉ ህጻኗን/ኑን/ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለቸውን/ውን ልጅ መጠየቅ። ሌሎች እርስዎን የሚያዩበት እንጂ መስማት የማይችሉበት ቦታ መሆኑን ማረጋገጥ።

አድርግ ዓይን ለዓይን መተያየት በሚችሉበት ከፍታ መቀመጦን ማረጋገጥ። ግልጽ የሰውነት ቋንቋን ይጠቀሙ።

አድርግ ሴቶች እና ወንዶች ልጆችን ተመሳሳይ ጾታ ካላት/ለው አዋቂ ሴት ወይም ወንድ ጋር መነጋገር ይፈልጉ እንደሆነ መጠየቅ።

አድርግ ህጻኗ/ኑ/ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለቸው/ው ልጅ ፀጥ ወዳለ ወይም ገለል ወዳለ ቦታ እንዲሄድ መምራት፣ ህጻኑን ያለ ፍላጎቱ ለብቻው ማቆየት።

አድርግ መንካት፣ ማቀፍ ወይም አካላዊ ንክኪ ማድረግ አሳቃቂ፣ ምቾት የማይሰጥ እና የሚያስጨንቅ ሊሆን ስለሚችል።

አዳምጥ

መደረግ ያለበት በንቃት ማዳመጥ እንዲሁም ቃላት አልባ ለሆኑ የሰውነት ተግባቦቶች ትኩረት መስጠት።

አድርግፍርድን ሳያስተላልፉ የሚነገረውን በመቀበል የተረጋጋ እና ታጋሽ መሆን።

አድርግህጻኑን / ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለውን / ቸውን ልጅ እራሳቸውን እንዲገልጹ እና የራሳቸውን ቃላት እንዲጠቀሙ ያድርጉ።

አታድርግ ቃለ-መጠይቅ ማድረግ ወይም መገምገም። ስለ ህጻኑ / ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ስላለው / ስላለቸው ልጅ ወይም ስላጋጠማቸው ነገር ማስታወሻ አይውሰዱ ፣ ፎቶግራፍ አያንሱ ወይም በቃል አይጋሩ።

አታድርግ ድንጋጤ ፣ አለማመን ፣ ቁጣ ወይም የህጻኗ / ኑን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለቸውን / ውን ልጅ ጭንቀት ሊያስከትሉ የሚችሉ ማናቸውም ሌሎች ምላሾችን ማሳየት።

አታድርግጠንካራ ቃላትን መጠቀም ወይም ከህጻኑ ወይም በጉርምስና እድሜ ካለው / ካለቸው ልጅ በላይ መናገር።

ምኞት

አድርግህጻኑ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው / ያለቸው ልጅ የነገርዎት / የነገረችዎት ነገር ችግር የሌለው ነገር መሆኑን ደግሞ ማረጋገጥ።

አድርግየህጻኑን አስተያየት ፣ እምነቶቹ እና ሀሳቦችን ማክበር ፡፡

አድርግለባህላዊ ሁኔታ ተስማሚ የሆኑ የማጽናኛ ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀሙ …

ምሳሌዎቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ:

አታድርግ የህጻኑን ደኅንነት ማረጋገጥ በእርሶ ቁጥጥር ያለ ነገር ባይሆንም ሊያደርጉት ስለማይችሉት ነገር <<ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል›› በማለት ቃል መግባት።

አታድርግ ህጻኑን / ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው / ያለቸውን ልጅ ባይፈልግም / ባትፈልግም ከእርስዎ ጋር መነጋገሩን / መነጋገሯን እንዲቀጥሉ ማስገደድ።

> “እምንሻለሁ / ሃለሁ” - እምነት መገንባት
>
> "የደረሰውን ነገር ስለነገርሽኝ / ከኝ ደስ ብሎኛል" -
>
> ከህጻኗ / ኑ ጋር ግንኙነትን መገንባት
>
> "የደረሰውን ነገር ስላካፈልሽኝ / ከኝ አመሰግናለሁ" -
>
> ርህራሄን ይገልጻል
>
> "ከእኔ ጋር ለመነጋገር በመፍቀድህ / ሽ በጣም ደፋር ነህ / ሽ" -
>
> ብርታት እና ድፍረት ይሰጣል

መስፈንጠርያዎች

አድርግህጻኗ / ኑ / ወይም በጉርምስና እድሜ ያለቸው / ው ልጅ የምትተማመንበት / የሚተማመንበት ሰው ካለ ይጠይቁ እንዲሁም ይህንን ሰው ማግኘት ወይም ለማግኘት የእርሶን አብሮነት የምትፈልግ / የሚፈልግ ከሆነ መጠየቅ።

አድርግእርሷ / ሱ ደህንነት እስኪሰማው ድረስ ወይም ስለደህንነቷ / ቱ ስጋት የማያድርበት / በት እና እምነት የምትጥልበት / የሚጥልበት ግለሰብ እንክብካቤ ስር እስከምትሆን / ሚሆን ድረስ ከህጻኗ / ኑ ወይም ከታዳጊዋ / ው ጋር መቆየት።

አድርግህጻኑ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው / ያለቸው ልጅ ለሚተማመንበትን / ለምትተማመንበት አዋቂ ስለሚሰጡ አገልግሎቶቹ እና እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ትክክለኛ እና ተገቢ መረጃዎችን መስጠት።

አድርግየሚያውቁትን እና የማያውቁትን ይናገሩ። የተጠየቀው መረጃ ከሌለዎት "እኔ አላውቅም" ወይም "ያ መረጃ የለኝም" ይበሉ።

አታድርግህጻኑን / ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለውን / ያለቸውን ልጅ ሲያወሩ ተንከባካቢያቸው እንዲኖር ማስገደድ ምክንያቱም ጥቃቱን የፈጸሙት እነዚህ ሰዎቹ ሊሆኑ ስለሚችሉ ወይም ህጻኑ / ኗ ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው / ያለቸው ልጅ ያጋጠማቸውን ነገሮቹ ለእነሱ ማጋራት ላይፈልጉ ስለሚችሉ።

አታድርግ ህጻኑን / ኗን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለውን / ቸውን ልጅ በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ / ና ለብቻ መተው (ለምሳሌ በለቅሶ ፣ በብስጭት ወይም በድንጋጤ ሁኔታ) ፡፡

አታድርግ ችግሩን ራስዎ ለመፍታት መሞከር ፣ እቅድ ማውጣት ወይም በህጻኑ ወይም በጉርምስና እድሜ ባለው / ባለቸው ልጅ ቦታ ሆነው ውሳኔ ማድረግ።

ለህጻናት ዕድሜ እና ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ ማጣቀሻ

ልምድ ያለው- ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከደረሰባቸው ህጻናት / በጉርምስና እድሜ ያሉ ልጆች ጋር የሰራ-ህጻናቱ እና በጉርምስና እድሜ ያሉትን ልጆች

ከራሳቸው ጋር እና እንክብካቤ ከሚያደርጉላቸው ጋር በመተባበር ውሳኔ ማድረግ ስለመቻላቸው ለመወሰን ትክክለኛ በታ ላይ እንዳለ ያስተውሉ።

ልዩ ባለሙያ ያልሆኑት የእርስዎ ሚና ህጻኑን ወይም በጉርምስና እድሜ ያለው / ያለቸው ልጅን ማዳመጥ እና ማፅናናት ፣ ከሚያምኗቸው ሰው ጋር ማገናኘት እና በሚገኙ የድጋፍ አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ መረጃን ማጋራት ነው። ከዚህ በታች ያሉት የዕድሜ ምድቦች ለማጣቀሻ ብቻ ሲሆኑ በዕድሜ ፣ በብስለት ደረጃ ፣ በእድገት ደረጃ እና በሌሎች ነገሮች አማካኝነት በመመስረት ሊለወጡ ይችላሉ።

15 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆኑ በጉርምስና እድሜ ያሉት ልጆች በአጠቃላይ የአእምሮ ብስለት ያላቸው ሲሆኑ

የራሳቸውን ውሳኔ ለመወሰን የሚችሉ እና የሚያደርጉትን ለመረዳት የሚችሉ ናቸው።

የእርስዎ ሚና: (1) በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጆች የደረሰባቸውን በደል ሲያካፍሉ ማዳመጥ ፣(2) በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጆች ቀጣይነት ላለው ድጋፍ ከሚያምኑት ሰው ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ ማገዝ እና (3) የድጋፍ አገልግሎቶች አቅርቦትን እና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል መረጃ መስጠት።

ከ 6 እስከ 9 ዓመት ያሉ ህጻናት እና ከ 10 እስከ 14 ዓመት ያሉ በጉርምስና እድሜ የሚገኙ ልጆች የደረሰባቸውን የጥቃት በደል በራሳቸው ሪፖርት ሊያደርጉ ወይም ማድረግ ላይችሉ ይችላሉ። ውሳኔዎችን በራሳቸው መወሰን ሊችሉ ወይም ላይችሉ ይችላሉ።

የእርስዎ ሚና:(1) በሚቀጥሉት እርምጃዎች እንዲያግዟቸው የሚያምኑትን አዋቂ ሰውን እንዲያገኙ ህፃኑኗን / ኑን / በጉርምስና እድሜ ያለችውን / ውን ልጅ ያግዙ እና (2) ለህፃኑኗ / ኑ / በጉርምስና እድሜ ላለቸው / ው ልጅ እና ለተመረጠው አዋቂ የድጋፍ አገልግሎቶች አቅርቦትን እና እነዚህንም እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ይስጡ።

ህጻናት እና ታዳጊዎች ከ 0 እስከ 5 ዓመት የግንኙነት ክህሎት ካለመኖር ወይም ውስን ከመሆን የተነሳ የደረሰባቸውን ጥቃት ራሳቸው ሪፓርት አያደርጉም። ሌላ ግለሰብ - ጓደኛ ፣ ተንከባካቢ ፣ የቤተሰብ አባል ፣ የማኅበረሰብ አባል ወዘተ - በልጁ ፈንታ እርዳታ ሊጠይቀ ይችላል።

የእርስዎ ሚና:በሚገኙት አገልግሎቶች እና እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃውን ለተጓዳኝ ግለሰብ መስጠት።

ከ UNHCR, Best Interest Determination Guidelines, 2008 የተወሰደ IRC / UNICEF, Caring for Child Survivors of Sexual Abuse, 2012. የተወሰደ።

ይህ መረጃ ለ 2015 IASC ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች መመሪያዎች አጋር የሚሆን መመሪያ ነው።

www.gbvguidelines.org

www.gbvguidelines.org/pocketguide

Camp Coordination and Camp Management

ጾታን መሰረት ስላደረገ ጥቃት በኪስ የሚያዝ መመሪያ